ሁለተኛው ዕቅድ ደግሞ ቪዛንቲን ዕቅድ የተባለው ነው ፤ ይኸም የቪዛንቲን ነገሥታት የመጀመሪያዎቹም ክፍተኞቹም ክርስቲያን ነገሥታት እንደመሆናቸው በርእሰ ከተማቸው በየጊዜው ታላላቅ አቢያተ ክርስቲያናትን በመሥራታቸው ራሱን የቻለ ቪዛንቲን የሚባል ዕቅድ ሊኖረው ቻለ። ይኸም ዕቅድ ቫሲልክ የተባለውን የያዘ ቢመስልም / በጉልላቱ/ የተለየ ቅርጽ ነበረው።

ሶሦተኛው በምዕራቡ ዓለም በካቶሊክና በፕሮቴስታንት ደግሞ ሌላ ራሱን የቻለ የቤተክርስቲያን ዕቅድ ተፈጠረ፤ ይኸውም 1ኛ ጊቲክ የተባለ ቀጥተኛ መስቀለኛ አሠራር ሆኖ በውስጡም በውጪም ከምሥራቁ ዓለም አሠራር ፈጽሞ የተለየ ነበረ።

አራተናው ባሮኪያ የተባለ ከንቲክ ዕቅድ የተለየ መልክ ያለው ነበር።

አምስተናው ከላይ የቆጠርናቸው ዓይነቶች ተደባልቀው ልዩ ዕቅዶች ተፈጠሩ። እነዚህም ዘመነ ተሀድሶን ፤ የሚያስታውሱ የክርስቲያን ቴክኒክና ርምጃን የሚያሳዩ ናቸው፤ ለምሳሌ የሮማው የቅዱስ ጴጥሮስ ቤተክርስቲያንና እርሱን የመሰሉ የሰውን ኅሊና ወደ አድናቆት የሚስቡ ሊሠሩ ቻሉ።

በኢትዮጵያ ክርስትና ከገባ ጊዜ ጀምሮ ልዩ ልዩ ዕቅድ ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ሲታነጹ ቆይተዋል። ስለ ዕቅድ ፤ ስለ ቤተክርስቲያኑ ክፍል ብዛት ማነስ፤ ስለበሮቹና መስኮቶቹ፥- ሌላም ይኽን ስለመሳሰሉት ግን የተወሰነ * ይኽ ነው የሚባል የተጠበቀና የተያዘ ዕቅድ ለመኖሩ መግለጫ አልተገኘም።

እንዲሁም በ 12 ኛው ምእተ ዓመት የተሠሩ የቅዱስ ላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ሥራዎች * እንዲሁም በ 14 ኛው ምእተ ዓመት እንደተሠራች የሚነገርላት የቅድስት የቤተልሔም (በጌምድር) ቤተክርስቲያን በቀጥታ ቫሲልካ ባይሆንም የቫሲልክ ዕቅድን ይዘው ይገኛሉ።

ቫሲልክ ማለት እንደ ብሉይ ኪዳን ቤተመቅደስ (ምኩራብ) ቅርጽ ሰቀላ ወይም ሞላላ ቅርጽ ነው። የዚህን ዓይነት ቤተክርስቲያን ቅርጽ የተወረሰው ከሰሎሞን ቤተመቅደስና ኋላም በዘመነ ክርስትና ታላቁ ቁስጠንጢኖስ እናቱ ንግሥት እሌኒ በኢየሩሳሌምና በቤተልሔም ከአሠሯቸው አብያተ ክርስቲያናት ቅርጽ ነው፤ ይህ የሰቀላ ቅርጽ ቤተክርስቲን በመጋረጃ ወይም በአእማድ እንጂ በግንብ የተከፋፈለ አይደለም። የንዑሰ ክርስቲያን ፤ የፍፁማን ክርስቲንና ዋናው መንበር ያለበት ቦታ የተለየ ነው። የሰቀላ ቤተክርስቲያን ጉልላቱ አንድ ብቻ አይደለም ፤ እንደ ትልቅነቱ ነው፤ የሰቀላ ቤተክርስቲያን በሩ የተወሰነ አይደለም። ሦስትም አራትም ከዚም በላይ ሊሆን ይችላል።

በእኛ ሀገር የተለመደው ሌላው ቅርጽ ክብ ነው። መቼ እንዴት እንደተጀመረ አይታወቅም እንጂ በመላ ኢትዮጵያ የሚገኙት አብዛኛዎቹ አቢያተ ክርስቲያናት ሁሉ ክብ (ቤተ-ንጎሥ) የሚባል ዕቅድ ያላቸው ናቸው። ዛሬም ሳይቀር በገጠር አዲስ ቤተክርስቲያን ሲሠራ በዚሁ መልክ መሥራትን ሕዝቡ ይወደዋል። ስለዚህ ይኸው ዕቅድ እንደ ቀጠለ ነው። እንደ ብዙዎቹ አነጋገር ከሆነ ጥንታዊው ዕቅድ ይኸው ክቡ ነው ይላሉ። ነገር ግን ይህ ሊሆን አይችልም ፤ ምክንያቱም ከላይ እንደዘረዘርነው ጥንታውያን ከሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ አንድም ክብ ሆኖ የተሠራ የለም።

ከአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ደግሞ ልዩ ልዩ ዕቅዶች መታየት ጀመረዋል። አንዳንዶቹ ክብነታቸውን ሳይለቁ ክብ ሆነው አራት መዓዘን ፤ ስድስት መዓዘን ፤ ስምንት መዓዘን እየሆኑ የተሠሩ አሉ ፤ ሌሎችም ዕቅዳቸው እንዲህ ነው ብሎ ግምት ለመስጠት የሚያስቸግሩ የተለየ ቅርጽ ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ ፤ አሁን ግን በብዛት ቫሲሊክ ወይም ቤዚንቲን ዕቅድ እየተስፋፋ መሄድ ጀምረዋል። በዚህም አብነት የሚሆኑት የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ የሰበታ ቅዱስ ገብርኤል & የአዋሳ ቅዱስ ገብርኤል & የደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለሃይማኖት ገዳም & የደብረ ጽጌ ቅድስት ማርያም ገዳም & የአክሱም ጽዮን አብያተ ክርስቲያናት ሕንፃዎችና እነርሱን የመሳሰሉ ሌሎችም አሉ።

ከእነዚህ ከሁለቱ ዕቅዶች ሌላ ዋሻ ቅርጽ አለ ፤ የዋሻ ቤተክርስቲያን በሩ ብዙ ጊዜ አንድ ብቻ ነው።

ቅዱስ ላሊበላ ከሠራቸው አብያተ ክርስቲያናት አንዳንዶቹ ዋሻዎች ናቸው። የዋሻ ቤተክርስቲን ጉልላት የለውም የመቅደሱም በር አንድ ነው።

ከላይ የተመለከትነው በዘመነ ክርስትና የሕንፃ ቤተክርስቲያን አሠራርን እድገት ነው። ከሥርዓተ ቤተክርስቲን አንፃር ይልቁንም የእኛ ሕንፃዎች የሚያሟሏቸው ሥርዓቶች አሉ። ከእነዚህም መካከል ሦስት ክፍል ያለው መሆኑ ፤ ቤተልሔሙ በምሥራቅ ብቻ የሚታነጽ መሆኑ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪም ስለ በሮችና መስኮቶች ራሱኝ የቻለ ሥርዓት አለ። ለምሳሌ ያህል የዋሻ ቤተመቅደስ ከመሬት በላይ እንደሚሠራው ሕንፃ እኩል የበር ቁጥር እንዲኖረው ባይታዘዝም የማይቀሩ ሥርዓቶች አሉ። ዋሻ በዓይነት ለየት ያለ ስለሆነ ከእነዚህ ጋር አይፈረጅም። ሌሎችን ስንመለከት ግን ራሱን የቻለ ውስጣዊ ሥርዓትም አላቸው። ለአብነት መቅደሱን (ቅድስተ ቅዱሳኑን) ብንመለከት ሁሉ ጊዜም ሦስት በር አለው። ሦስቱ በሮችም በምዕራብ እና በሰሜንና በደቡብ ብቻ ሲሆኑ የምሥራቁ ግን መስኮት ብቻ ይኖረዋል። ይህም ሰው የማይገባበትና የማይወጣበት ሰሎሞንም ቤተመቅደሱን ከሠራ በኋላ ዘግቶት የኖረ በመሆኑ እስካሁን ድረስ በቤተክርስቲያናችን < የሰሎሞን በር> እየተባለ ይጠራል። ቅኔ ማኅሌቱና ቅድስቲቱም ቢሆኑ ግን ቢያነስ ሦስት የተለያዩ በሮች ያስፈልጓቸዋል። እነዚህም ሦስት ዖታ < ካህናት &ወንዶችና ሴቶች) የሚገቡባቸው ናቸው። ከዚህ አንፃር ሦስቱ ክፍሎች እያንዳንዳቸው አጠር አድርገን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

3.3 <u>የቤተክርስቲያን ክፍሎች</u>

ማንኛውም ቤተክርስቲን በተለያየ ዕቅድ ቢሠራም **3 (ሦስት)** ክፍል አለው ፤ ይኸውም በሰሎሞን ቤተመቅደስ አምሳል መሆኑ ነው & ምክንያቱም ለብዙው ክርስትና እምነት ሥርዓት መሠረቱና ምሳሌው የብሉይ ኪዳን ሥርዓት ነው። እንግዲህ ለቤተክርስቲያናችን ሦስት ክፍሎች አሉት ስንል የእያንዳንዱ ክፍል አቀማመጥና ጥቅም ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

ሀ. <u>ቅኔ ማኅሌት</u> ፡- የመጀመሪያ ክፍል ወደ ቤተክርስቲን ሲገቡ የሚገኘው ዙሪያው በመላ ቅኔ ማኅሌት ይባላል። ስያሜው ከግብሩ የተወረሰ ነው። ምክንያቱም ሥርዓተ ማኅሌት ይከናወንበታል።

በቅኔ ማኅሌት በመስዕ (ሰሜናዊ ምሥራቅ) በኩል ቀሳውስትና ዲያቆናት በመንፈቀ ሌሊት በነግህ ሰዓታት ይቆሙበታል ፤ ኪዳን ያደርሱበታል ፤ በጥንት ቤተክርስቲያን ሥርዓት ሥርዓተ ጥምቀት የሚፈጽሙት በዚሁ ክፍል ነበር። ለጥምቀተ ክርስትናና ለቁርባን ያልበቁ በተምህርት & በንሰሀ ገና የሚፈተኑ ሐዲሳን አማንያንም (ንዑሰ ክርስቲያን) ዲያቆኑ <ባኡ ንዑሰ ክርስቲን > እሰከሚል ድረስ በዚያ ይቆያሉ & ዲያቆኑ < የክርስቲያን ታናናሾች ውጡ> ብሎ በደወል ሲያውጅ ወደ መካነ ቀኖናቸው ተመልሰው ይሄዳሉ ወንዶችም ምእመናንም ቆመው የሚያስቀድሱት በዚህ ቦታ ነው።

መዘምራን በሚዘምሩበት በቅኔ ማኅሌት ቆመው የሚያስቀድሱ ንፍቀ ዲቆናት አናጉንስጢስ & መዘምራን ናቸው። (ፍት. መን. አንቀጽ 9)።

<u>ለ. ቅድስት፡-</u> ስያሜው ከብሉይ ኪዳን ስያሜ ጋር ተመሳሳይ ነው። የቤተክርስቲያኑ መዕከላዊ ቦታ ነው። በዚህ ክፍል በስተምዕራብ በኩል ቆመው የሚያስቀድሱት ቆሞሳት ቀሳውስትና ዲያቆናት ናቸው ፤ በስተሰሜን በኩል መነኩሳትና የሚቆርቡ ወንዶች ምእመን & በስተደቡብ በኩል ደናግል መነኩሳይት & የካህናት & የዲያቆናት ሚስቶችና የሚቆርቡ ምእመናት ቆመው ያስቀድሱበታል፤ በዚሁ ክፍል ቆመው ላስቀደሱ ምእመናን ሥርዓተ ቁርባን ይፈጸማል። ከሥርዓተ ጥምቀትና ከሥርዓተ ንሰሐ በስተቀር የሌሎች ምሥጢራተ

ቤተክርስቲን ሥርዓተ ጸሎት የሚፈጸመውም በዚሁ ክፍል ነው። በዚሁ ክፍል ክህነት ሊሰጥበት (ምሥጢረ ክህነት ጸሎት ሊጸለይበት) & ምሥጢረ ተክሊልና የምሥጢረ ቀንዲልም ጸሎት የሚጸለይበት ክፍል ነው። ቅድስቱም በምሥራቅ & በምዕራብ & በሰሜንና በደቡብ አራት በሮች ሊኖሩት ይገባል።

<u>ሐ. መቅደስ፡-</u> የዚህ ስያሜው ከብሉይ ኪዳን ቤተመቅደስ የተወረሰ ነው፤ በዚህ ውስጥ ምሥጢረ ቁርባን & ሥርዓተ ቁርባን ይፈጸምበትል & መንበረ ታቦቱ ሌሎችም ንዋያተ ቅድሳት ይገኛሉ። በዚህ ክፍል ከርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ሊቃነ ጳጳሳት & ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ያስቀድሳሉ። ወደዚህ ክፍል መግባት የሚችሉ ካህናትና ዲያቆናት ብቻ ናቸው። መቅደሱ 3 (ሦስት) በር አለው። ይህ በር በምዕራብ & በሰሜንና በደቡብ ነው፤ ለእያንዳንዱ በር መንጦላዕት (መጋረጃ) አለው። የዚህ ኣይነት ቤተክርስቲያን ባለአንድ ጉልላት ነው ።

3.4 <u>በቤተክርስቲያን ዙሪያ የሚሠሩ አገልግሎት የሚሰጡ ቤቶች</u>

ቤተክርስቲያን ሲሠራ የሚሠራው አንድ ቤት ብቻ አይደለም። በቤተክርስቲያን ሊሠሩ የሚገባቸው ከቤተክርስቲያኑ ጋር አብረው አገልግሎት የሚሰጡ ቤቶች አሉ።

በቤተ ክርስቲያን ምሥራቅ ዲያቆናቱ ለመሥዋዕት የሚሆነውን ሕብስትና ወይን የሚዘጋጅበት ሁለተኛ ቤት ይሠራል። ይህ ቤት ‹ ቤተልሔም › ይባላል። ስያሜው የተወሰደው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት በቤተልሔም ዘይሁዳ ምሳሌ ነው። ምሥጢሩንና ቁም ነገሩ ደግሞ ዲያቆናት ሕብስቱንና ወይኑን በቤተልሔም አዘጋጅተው ወደ ቤተክርስቲያን ለመሥዋዕት ማምጣታቸው በቤተልሔም የተወለደው፤ በቀራንዮ ለመሥዋዕት የቀረበው ክርስቶስ ይህ ነው ለማለት ነው። መቅደስ የቀራንዮ ምሳሌ ነው።

ለመሥዋዕት የሚቀርበው (መገበሪያ) የሚሰየምበት ፣ በቤተክርስቲያን ቅጽረ ግቢ የሚሠራ ሦስተኛ ቤት አለ። ይህም ‹ የግብር ቤት› ይባላል። ስንዴው መገበሪያ ተብሏልና። መገበሪያው አሰናድቶ ማቅረብ ደግሞ መሰየም ይባላል። ይህም የመሥዋዕቱ አቀራረብ ቋንቋ ነው።

የቤተክርስቲያን ንዋየ ቅድሳት የሚቀመጡበት አራተኛ ቤትም ይሠራል፤ ይህም ዕቃ ቤት ይባላል። የቤተክርስቲያኑ መገልገያ የሆኑ አልባሳትም ፣ መጽሐፍትም የሚጠበቁት በዚሁ ቤት ነው። / ሕዝ 44*19 ፣ ፍት መን 12/

ሥርዓተ ጥምቀት የሚፈጸምበት የማጥመቂያ ቤትም አለ። ከዚህ ሌላ በገጠር ባሉ አብያተ ቤተክረስቲያናት የሙታን በድን የሚያርፍበትና ጸሎተ ፍትሐት የሚፈጸምበት ደጀ ሰላም ከቤተክርስቲያኑ ቅጽር ተያይዞ ይሠራል።

ከዚህ በታች የተጠቀሱት 5 ቤቶች በግድ ከቤተክርስቲያኑ ሳይለያዩ አብረው የሚሠሩ አስፈላጊ ቤቶች ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ እንደ ምእመናን ዕቅም ሊሠሩ የሚገባቸው ቤቶች አሉ። እነዚህም፡-

1. የሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት
2. የሰንበት ትምህርት ቤቶች ክፍሎች
3. የስብከተ ወንጌል አዳራሽ

4. የእንግዶችና የካህናት ማረፊያ ቤቶች
5. የመንፈሳዊ ትምህርት ቤትና የተግባረ እድ መማሪያ ክፍሎች
6. ቤተ መጻሕፍት
7. የንዋየ ቅድሳትና ጧፍ ዕጣን መሸጫ ክፍሎች ናቸው።

3.5 ታቦት / ጽላት/ እና መስቀል

ቅዱስ ጳውሎስ ደጋግሞ እንደተናገረው ፍጹምና አማናዊ የሆነ መምጣቱ እንደ አዲስ የምትቆጥረውን ኦሪትን አስረጅቷል። 2 ኛ ቆሮ 3*7-11። ይህም ንጽጽራዊ አገላለጥ ምሥጢራዊ ነውና ማስተዋል ይገባል። በሌሊት ደምቃ ስታበራ ያደረች ጨረቃ በቀን እንደ ማታው የማታገለግለው ከእርሷ የበለጠች ፀሐይ በመውጣቷ እንጂ ጨረቃ በመወገዷ አይደለም። ይልቁንም በቀን ሰዓት ጨረቃ ለራሷም የሚያስፈልጋትን ያህል ከፀሐይ / ከምትበልጣት/ ትቀበላለች፤ የብሉይ ኪዳንና የሐዲስ ኪዳንም ሥርዓት ፀሐይና ጨረቃን የሚመሳሰሉበት መንገድ አላቸው። የመጀመሪያው የፀሐይ ብርሃን ድምቀቱን ጨረቃን እያለች የሌለች የሚያስመስላትን ያህል ከብሉይም የተቀበልናቸው እያሉ ከፀሐይ ክርስቶስ ካገኘነው ጉልህ / ፍጹም/ ጸጋና ደኅንነት የተነሳ የሌለ የሚመስሉ ሊኖሩ ይችላሉ። ሁለተኛው ደግሞ ፀሐይ ለጨረቃ ብርሃን እንደምትሰጣት ከፀሐየ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ በተደረገው ቸርነት በተፈጸመው ድኅነት ኃይልና ከብር አግኝተው እንደ ብርሃን የሚበሩ መኖራቸው ነው። እንደዚህ ዓይነት ምሥጢራትን ከሚያስተላልፉ ንዋያተ ቅድሳት መካከል ታቦት /ጽላት/ ተጠቃሽ ነው። ከዚሁ ጋር አያይዘን መስቀልን አብረን እንመለከታለን።

3.5.1 ታቦት ወይም ጽላት

ታቦት ከብሉይ ኪዳን ከእስራኤል የነፃነት ሕይወት ጋር የተያያዘ ታሪክ አለው። በአሁኑ ጊዜ የጻህሉና የጽዋው ማስቀመጫ ፤ የመሥዋዕቱ ማክበሪያ ታቦት ወይም ጽላት ይባላል። ኢትዮጵያ ከብሉይ ኪዳን ከወሰደችው አንዱ ጽላተ / ታቦተ ሕግ/ ነው። በኢሪት ታቦት የሚባለው ጽላቱ የሚቀመጥበት ማኅደሩ ነው። / ዘጸ 40 *26 ፤ 25* 22 ፤ መዝ 130* 8 2 ቆሮ 6*16 ፤ ዕብ 9*4 ፤ ራእ 11*19/። የታቦት ትርጓሜው ማደሪያ መሠወርያ ማለት ብቻ ሳይሆን መታያ መገለጫም ነው። ታቦት የእግዚአብሔር መገለጫ ነውና ። / ዘጸ 13 *21-22/

ጽላት የሚባለው እግዚአብሔር ለሙሴ አስቀድሞ አሠርቱ ቃላትን በእጁ ጽፎ የሰጠው ቃሉ ተጽፎ የሚከኝበት ነው። / ዘጸ 4*13 ፤ 5*1-22 ፤ 31*18 ፤ 24*12 ፤ 25*16 ፤ 10*1-6 ፤ 34*1-29/።

ይህ በብሉይ ኪዳን የነበረው ሥርዓት ነው ፤ በሐዲስ ኪዳን ጽላትም ታቦትም ያው አንዱ ምሥዋዕ ነው። ከላይ በመግቢያው በገለጽነው መሠረት አካላዊ ቃል በመጣ በተገለጠ ጊዜ በሰሌዳ ላይ የተጻፉት ቃላት በመጻሕፍት ተጽፈው ለሕግነት ከማገልገል ብቻ ተወስነ። እነዚህ ቃላት ለኦሪት መሠዊያ በተቀመጠው ታቦት ውስጥ ነበሩና። በሥጋ የተገለጠው አካላዊ ቃል ግን ራሱ መሥዋዕት ስለሆነ የጽላቱና የታቦቱ አገልግሎት በቀን እንዳለች ጨረቃ ሆነ። ይህም አዲስ ብርሃን ተቀብለው / ሥርዓት ተሠርቶላቸው/ ለተሻለ አገልግሎት ለመታደል በቁ። በዚህ መሠረት ሁለትነታቸው ጠፍቶ በአንድነት እንዲዘጋጁና ለክቡር የክርስቶስ ሥጋና ደም ማክበርያ ሆኑ። ጥንቱንም ታቦት ማለት የእግዚአብሔር

ማደሪያ ማለት ነውና። ይህንን ጉዳይ ሌሎች እኅት አብያተ ክርስቲያናት ‹ መሠዊያ› / Altar/ በማለት ያዘጋጁታል ፤ ክብሩም ልዩ ነው። ከዚህ ይልቅ እኛ መንበረ ታቦት ያለን በመሆኑ በእውነት ያለሐሰት የሚሻል ነገር እንዳለን መናገር እንችላለን። /ሁሌ ኪዳናት ገጽ 310-314 ተመልከት።/

ከዚህ በኋላ በጽላቱ ላይ ‹ አልፋ ወዖ ቤጣ የውጣ› የሚለው የጌታ ስም ይቀረጽበታል ፤ ከላይ ሥዕለ ሥላሴ ቀጥሎ ምሥለ ፍቁር ወልዳ ፤ ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ እንዲሁም መቅደሱ የተሠራለት ጻድቅም ሆነ ሰማዕት ፤ መልአክም ሆነ ሐዋርያ ፥ ሥዕሉ ይቀረጻል ፤ ስሙ ይጻፋል። ይህ ከተጻፈበት በኋላ በኤጲስ ቆጶስ እጅ ተባርኮና ሜሮን ተቀብቶ በመንበሩ ይሠየማል።

ጽላተ ኪዳኑ ማኅደረ እግዚአብሔር ነው ፤ ያለ ታቦትም መሥዋዕት አይሠዋም። በቅዳሴ ጊዜ ኅብስቱንና ወይኑን ወደ ቤተመቅደስ ሲገባ ቄሱ ሥርዓተ ቅዳሴውን የሚያከናውነው ኅብስቱን ሥጋ መለኮት ወይኑን ደመ መለኮት ወደ መሆን የሚለውጠው መዚህ በታቦቱ ላይ ነው። ይህም የአሁኑ ታቦት በክብር የላቀ መሆኑን ያስረዳናል። የቀደመው ታቦት የበግና የፍየል ደም የሚረጭበት ነበርና። የአሁኑ ግን የክቡር የክርስቶስ ሥጋና ደም ይቀርብበታል።ለዚያኛው ይህ የሚያስፈልገው ከሆነ ለዚህ ለፍጹሙ መሥዋዕትማ ይልቁን እንዴት አብልጦ አያስፈልገው።

3.5.2 መስቀል

‹ ኮነ ብእሴ ወረሰቅለ በእንቲአነ በመዋዕለ ጲላጦስ ጴንጤናዊ ሐመ ወሞተ ..... ፤ ሰውም ሆነ ስለእኛም ተሰቀለ .....› ተብሎ በቀኖና ሃይማኖት እንደ ተጻፈው ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ሆኖ ምንም ሳይበድል በበደለኛው ሰው እግር ጉብቶ ሞተ ፤ ሞቱም በመስቀል ሆነ። ወልድ ሰው የሆነበት ዋናው ዓላማ ለእኛ ለሰዎች ቤዛ ለመሆን ተላልፎ ለመሞት ነውና ‹ ስለእኛ ተሰቀለ› አለ። በአዳም በደል ምክንያት በመላ የሠው ነገድ ለሞት ተዳርጎ ነበር፤ ስለዚህ ወልድ በለበሰው ሥጋ መከራ መሥቀልን ተቀብሎ የሰውን ነገድ ነፃ ያወጣው ዘንድ ተሰቀለ።እውነተኛና የማዳን ችሎታ ያለውን መሥዋዕት ያቀረበው ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን መስቀሉ ደግሞ ሥጋው የተፈተተበት እና ደሙ የፈሰሰበት መንበር ሆነ ፤ እውነተኛ መሠዋዕት ሆኖ በመስቀል መንበርነት የተሠዋው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ክርስቶስ የራሱን ደም አፍስሶ ሥጋውንም ቆርሶ ራሱን ክሶ የሰውን ልጅ ሁሉ ከአባቱ ጋር ያሰታርቅ ዘንድ ጎሩይ ማዕከለ እግዚአብሔር ወሰብእ ሆኖ ተሰቀለ። / 2 ኛ ቆሮ 5*19/

ሕግን በመተላለፋችን የእግዚአብሔር ጠላቶች ሆነን ነበር፤ ስለዚህ ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ አልቻልንም ነበር ፤ ነገር ግን ክርስቶስ በመልዕልተ መስቀል በመስቀሉ እኛን አስታረቀን ፤ በመስቀሉም ኃጢአትን ቀጣው ፤ ቸነከረው ፤ ሰቀለውም። / ኤፌ 2-15-16/።

በእንጨት / በዕጽ/ ምክንያት የመጣውን በደል ክርስቶስ በእንጨት / በእጸ መስቀል/ ላይ ተሰቅሎ አጠፋው።

ወልድ ከሰማየ ሰማያት መውረዱ ከሰው ወገን መወለዱ ፥ ራሱን በፈቃዱ ዝቅ ማድረጉ ሲሆን ከዚህ የበለጠ ደግሞ ሞቱን በመስቀል አደረገው። ወልድ የእኛን ውርደት ያስወግድ ዘንድ መርገማችንንም ያርቅልን ይደመስስልን ዘንድ በመስቀል ተሰቀለ ፤ በመስቀል ተሰቅሎ የሚሞት ሁሉ ርጉም ይባል እንደነበር የሕገ ኦሪት ተቀባይ ሙሴ ሬሳው በእንጨት ላይ አይደር ፤ ነገር ግን በዚያው ቀን ቅብረው ፤ በእንጨት ላይ የተሰቀለ ሁሉ ከእግዚአብሔር ተረግሟልና› ሲል ገልጦ ጽፎአል። / ዘዳ 21*23/ ቅዱስ ጳውሎስም ክርስቶስ ርግማንን ከእኛ ያርቅ

ዘንድ በመስቀል ተሰቅሎ ሞተ። / ገላ 3*13/ ብሏልና። ክርስቶስን ወንጀለኛ ለማስመሰል ከወንጀለኞች ጋር ሰቀሉት። ይሁን እንጂ ሕግን ሳያፈርስ ወንጀልንም ሳይሠራ ቢሰቀል ሞቱ ለእኛ መድኃኒት ሆነን። ይህም በመስቀል የሆነው ሞቱ የአዳምን በደል ከፍተኛነት አስከፊነትንም ያሳያል።

መስቀል በጥንት ግብሩ የርግማንና የኃጢአት ምልክት ሆኖ መቆየቱ ቢታወቅም አሁን የርግማን ምልክት የነበረው ተሽሮ የድኅነት ምልክት የሕይወት አርማ ሆኑአል። ግበረ ሠላም በመስቀሉ ፤ ክርስቶስ ሠላምን በመስቀሉ አደረገ› እንዳለው የድኅነት ሥራ የሠራበትን ክቡር ደሙ ያፈሰሰበትን መስቀሉን የሠላማችንና የድኅነታችን አርማ አድርገን እንይዘዋለን ፤ እናከብረዋለን። /ቆላ 1*19-20/ ። ምክንያቱም የክርስቲያኖች መመኪያና አለኝታ ፥ መከታና የድል ምልክት ነውና። ‹ እኔ ግን *ለእኔ ግን ጌታ ከተሰቀለበት ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ የምመካበት ነገር የለኝም› ብሎ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አስተምሮአል። /ገላ 6*14/። ስለሆነም መስቀል በቤተክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ክብር አለው።

ስለዚህም መስቀሉም እንሸከማለን። እነ ቆስጠንጢኖስ በብርሃን ቅርጽ ያዩት ይህ መስቀል የፍርድ ምልክት ሆኖ ይኖራል።

ለክርስቶስ መስቀል የተለየ ክብር የምንሰጥበት የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። እነሱም፦

1. ክርስቶስ መሥዋዕት ሆኖ ራሱን የሠዋበት አውነተኛ መንበር በመሆኑ
2. የክርስቶስ ደም የፈሰሰበት ፥ እኛ የዳንበት የነፃነት አርማችን ፥ የእኛ የክርስቲኖች አንድነት የተመሠረተበት የድኅነት አርማችን ነው።
3. መስቀል መለኮታዊ ፍቅር የተገለጠበት መሣሪያ ነው ፥ ማለት የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ ክርስቶስ ስለኛ መከራ መስቀልን ተቀብሎ በእርሱ ውርደት እኛ ከብረናል ፥ ይህ የመጨረሻ ፍቅሩን የገለጠበት መስቀል ስለሆነ እናከብረዋለን።
4. መስቀል ለአመንበት ኃይላችን ነው። ይህ የመስቀል አማናዊና ምሥጢራዊ ኃይል ቅዱስ ጳውሎስ እንደ አለው ላመኑ ነው እንጂ ላላመኑ ሞኝነት ነው። 1ኛ ቆሮ 1*18 እንዲያውም መስቀልን ‹ ኃይለ እግዚአብሔር ነው› ማለቱ ዋዛ ይመስላቸዋል።መስቀልን በመቅጫነቱ የሚመለከቱት ብዙ ናቸው ርግጥ መስቀሉ ለሞት ፥ ለአጋንንት መቅጫ ሆኗል።

መስቀል በብሉይ ኪዳን ብዙ ምሣሌ አለው ፤ የኖሕ መርከብ የተሠራችበት እንጨት ሙሴ የፈርኦንን ጠንቋዮች ድል ያደረገበት በትር የመስቀል ምሳሌዎች ናቸው። ምእመናን በክርስቶስ አምነው በመስቀል አማትበው ከኃጢአት ከአምልኮ ጣዖት ድነዋል። በመስቀል አጋንንትን * መናፍቃንን ፥ ፍትወታት እኩያትን ድል ሲያደርጉ ይኖራሉ።

መስቀልን ሁልጊዜ አርማችን አድርገን በፊታችን እናቆማለን። ይህንንም አርማ በተመለከትን ጊዜ ትዝ ሊሉን የሚገቡ ነገሮች ፦-

1. መስቀል የውርደት፥ የርግማን ምልክት የነበረ ሲሆን ክርስቶስ ስለኛ መሥዋዕት በመሆን ለበረከት እንዳደረገው እንገነዘባለን።
2. መስቀል ታላቅ የፍቅር ምልክት ሁኖ ክርስቶስ ስለ እኛ በመስቀል ከሞተ እኛም ይህንኑ መስቀል የፍቅር ምልክት አደርገን እንድንሸከመው የክርስቶስንም ፍጹም ፍቅር እንድንረዳውና ለፍቅሩ ተገቢ የሆነ ሕይወት እንዲኖረን እንዲሁም እኛም እርስ በራሳችን በፍጹም ፍቅር መዋደድ እንዲገባን ያሳስበናል።

‹ መስቀሉን ተሸክሞ በኋላዬ ያልተከተለኝ እኔን ለማገልገል አይገባውም› ሲል ክርስቶስ የሰጠው ለክርስትና ሕይወት ወሳኝ መሆኑን መገንዘብ አለብን። / ማቴ 18/

ስለዚህ መስቀሉን በተመለከትን ቁጥር በመስቀል የተሰቀለውን መድኃኒታችንን ክርስቶስን እናስታውሳለን።

የክርስቶስ ሞቱን ስናስታውስ ሞቱ በመስቀል ነውና ለእኛ ሞቱን እናስባለን ማለት ነው።

የዘላለም ሕይወት የምናገኝበት * ሥጋው የተፈተተበት ፣ ደሙ የፈሰሰበት መስቀል ነው ፣ ከዚህ የተነሳ መስቀል ከዓይነ ሥጋችንም ከዓይነ ነፍሳችንም ሊርቅ አይገባውም። / ዮሐ 3*15 ፤ዘኁ 21*8-9/።

መስቀል እግዚአብሔርና ሰው የታረቁበት ታላቅ አደባባይ ነው ፤ ክርስቶስ መስቀልን ለአዳም እውነተኛ ፍርድን ያደረገበት አደባባይ ሲሆን እንከብርበታለን እንመካበታለን እንጂ አናፍርበትም ። ከዚህ የተነሳ የቤተክርስቲያን ምሥጢራትን ለመፈጸም መስቀል ከፍተኛውን ቦታ ይዞ እንመለከተዋለን። የመጀመሪያውና ዋናው ቡራኬ የሚከናወነው በመስቀል ነው። ይህ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ነው።ስለዚህ በቅዳሴም ጊዜ ሆነ በሌሎች የማኅበር ጸሎት ጊዜያት ያለ መስቀል ቡራኬ አይከናወንም። ካህናቱም ሙሴና አሮን ሕዝቡን በባረኩት በረከት የሚባርኩት በእጅ መስቀል ነው። እኛም ሁል ጊዜ ገጻችንን ባማተብን ጊዜ / የመስቀል ምልክት ባደረግን ጊዜ/ እግዚአብሔር ወልድ በአባቱና በእኛ መካከል እርቅ የፈጸመበት መሣሪያ እንደሆነ ይሠማናል ፤ ስለዚህ መስቀል የክብራችን ምልክት ነው ፤ መስቀል ጌጣችን ነው።

እንግዲህ ይህንን ሁሉ አብነት ነስተን መስቀልን እናከብራለን። አርማችን አድርገን እንሸከማለን ፤ በመንኖርበት በምንሄድበት ሁሉ የመስቀሉን ምልክት እናደርጋለን። በመስቀል የዳንን መሆናችንን እንመሰክራለን። መስቀሉን መሳለም ብቻ ሳይሆን እንሰግድለታለን። / መዝ 130*7/

ክርስቶስ ንጽሐ ባሕርይ ሆኖ ሳለ እኛን ለማዳን በፈቃዱ ብዙ ህማም በአይሁድ ከተቀበለ በኋላ ሞተ ፤ ሞቱም በመስቀል ነው። ከዚህ የተነሳ የክርስቲያኖች ኪነ-ጥበብ ሁሉ ምልክቱ መስቀል ሆነ ፤ በልብሳቸው ፣ በመጽሐፋቸው ፤ በቤት ዕቃቸው ሁሉ የመስቀል ምልክት አለበት። በብዙ አገሮች ይልቁንም በመካከለኛው ምሥራቅ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ክርስቲያን መሆናቸው የሚታወቀው በክንዳቸው ፤ በመዳፋቸው በሚጠቀሩት / የሚነቀሱት / የመስቀል ቅርጽ ነው። ባልታወቀ ቦታ ሄደው ክርስቲያን ነን ለማለት ሲፈልጉ ያንን ብቅ አድርገው ያሳያሉ።

በሀገራችንም ጥልፉ * ዝምዝሙ ፤ ጌጣጌጡ * ሌላ ቀርቶ ሴቶቹ በግንባራቸውና በሌላም አካላቸው በመስቀል ቅርጽ ይጠቀራሉ / ይነቀሳሉ/። በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ብቻ ሳይሆን ከሞቱም በኋላ መስቀል ከምእመናን አይለይም። አጽማቸው በሚያርፍበት በመቃብራቸው ላይ ሁሉ የመስቀል ቅርጽ ከዕፅ ወይም ከድንጋይ ይሠራል። በመቃብራቸው ላይ መደረጉ ፤ መስቀል የሞትና የመከራ ምሳሌ መሆኑ ቀርቶ የትንሳኤና የሕይወት ምልክት መሆኑን ለመግለጥ ነው።

የመስቀል ክብር ከላይ እንደተገለጠው ከፍተኛ ስለሆነ መስቀል በደረት ላይ ፣ መስቀል በጣት ላይ ፣ መስቀል በየልብሳችን ላይ ፣ መስቀል በአብያተ ክርስቲያናት አልባሳት ላይ ፣ መስቀል በአብያተ ክርስቲያኑ በርና መስኮት ላይ ፣ መስቀል በየጳጳሳቱና ቀሳውስቱ እጅ ላይ ይገኛል።

ስለዚህ መስቀል ኃይላችን ፣ መስቀል ብርታታችን ፣ መስቀል ቤዛችን ፣ መስቀል የነፍሳችን መድኃኒት ነው። አጠቃቀሙ ግን ከላይ በተገለጠው መሠረት ሥርዓትን የተከተለ ነው። የእጅ መስቀል ለካህናት / ለቀሳውስትና ከዚያ ላሉ ባለሥልጣናት/ ብቻ መሆኑ የሚዘነጋ ሥርዓ አይደለም።

3.6 . የንዋየተ ቅድሳት ምሥጢራዊ ትርጉም የአቀማመጥና የአጠቃቀም ሥርዓት

ቤተመቅደሱንና በቤተመቅደሱ ውስጥ ካሉት የከበሩ ንዋያተ መካከል ያለ እነርሱ፡- ቅዳሴ መቀደስ የማያስችሉትን ዋና ዋናዎቹን ታቦትና መስቀል ቀደም ብለን ተመልክተናል። በቤተክርስቲያን ያሉ ንዋያት ግን እነዚህ ብቻ አይደሉም። በመሆኑም ከላይ ከተገለጹት ውጭ ያሉትን / የሚገኙትን/ ንዋያት ምንነትና አገልግሎት እንዲሁም የአጠቃቀም ሥርዓት እንመለከታለን።

3.6.1 <u>መብራት፡-</u> መብራት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ƒ ውፊት አለው።

እግዚአብሔር ለሙሴ በሠራለት ሥርዓት በሰጠው ትእዛዝ ‹ ከመጀመሪያው ወር / ሚዝያ/ በፊተኛው ቀን / መባቻ/ የመገኛኛውን ድንኳን ማደሪያ ትተክላለህ ፤ በእርሱም ውስጥ የምስክሩን ታቦት ታኖራለህ ፤ታቦቱንም በመጋረጃ ትጋርዳለህ ፤ ገበታውንም አግብተህ በእርሱ ላይ የሚኖረውን ዕቃ ታሰናዳለህ› ካለው በኋላ ‹ መቅረዙን አግብተህ ቀንዲሎቹን ትለኩሳለህ› ብሎ ነግሮታል / ዘጸ 40*2-4/።

መቅረዝ ማለት የሻማ ማብሪያ ነው ፤ ቀንዲል የሻማ ወይም የዘይት መብራት ነው።

ሙሴም ከእግዚአብሔር እንደታዘዘ ‹ መቅረዙን በመገኛኛው ድንኳን ውስጥ በገበታው ፊት ለፊት በማደሪያው በደቡብ በኩል አኖረ ፤ ቀንዲሎቹም በእግዚአብሔር ፊት ለኮሰ /አበራ/ ።/ዘጸ 24*24/።

በዚሁ ትውፊትና ምሳሌነት በቤተክርስቲያን የሚበራው መብራት ጡዋፍና ዘይት ነው።/ ፍት.መን አንቀጽ 1/። የዘይቱ መብራት ቀንዲል ይባላል፤ ቀንዲል / ካንድል/ የላቲን ቃል ነው። ፍቺው መብራት ማለት ነው። መብራቱም የወይራ ዘይት ነው።

በቤተክርስቲያን ብዙ መብራት ማብራት ታዟል። በተለይ ቅዱሳት መጻሕፍት ማለት መልዕክተ ጳውሎስ ፣ መልክታተ ሐዋርያት ፣ ግብረ ሐዋርያት ሲነበቡ በቤተክርስቲያኑ በጣም የበራ እንዲሆን ታዟል። ይልቁንም ወንጌል ሲነበብ እጅግ በጣም መብራት ማብዛት እንደሚገባ ተሠርቷል። / ፍት.መን አንቀጽ 1/።

3.6.2<u>አልባሳት</u>

የአልባሳት ስምና ዓይነት

1. <u>የቀሳውስት ልብስ</u>፡- መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትውፊትና ምሳሌ አላቸው።በኦሪት ሙሴ‹ አሮንና ልጆቹ ወደ መገናኛው ድንኳን ደጅ አፍ አቅርበህ በውኃ ታጥባቸዋለህ ፤ የተቀደሰውንም ልብስ አሮንን ታለብሰዋለህ በክህነት ያገለግለኝ ዘንድ ቀብተህ ትቀድሰዋለህ ፣ ልጆቹንም አቅርበህ ሸሚዞችን ታለብሳቸዋለህ ፤ በክህነትም ያገለግለኝ ዘንድ አባታቸውን እንደ ቀባህ ትቀባቸዋለህ› ተብሎ ለሙሴ ሥርዓት ተሰጥቶታል። / ዘጸ 40*12-16/

‹እግዚአብሔርም ሙሴን እንዳዘዘው በመቅደሱ ለማገልገል ከሰማያዊ ከሐምርዊ ከቀይ ግምጃም በብልሃት የተሠራ ልብስ ለአሮንም የተቀደሰውን ልብስ አደረጉ ፤ እግዚአብሔርም ሙሱን እንደ አዘዘው ኤፋዱን ከወርቅ ከሰማያዊም ከሐምራዊም ከቀይ ግምጃም ከተፈተለም ከጥሩ ግምጃም አደረገ ፤ ..... እንደ ሸማኔ ሥራ ከጥሩ በፍታ ለአሮንና ለልጆቹ ሸሚዞች ፥ ከጥሩ በፍታም መጠምጠሚውን ከጥሩ በፍታም መልካሞችን ቆቦች ከተፈተለም ከጥሩ በፍታ የእግር ሱሪዎችን ከተፈተለም ከጥሩ በፍታም ከሰማያዊም ከሐምራዊም ከቀይ ግምጃም ከጥልፍ አሠራር ሠራ መታጠቂያውን አደረጉ› ይላል። /ዘጸ 39*1 እስከ መጨረሻው/።

በዚሁ ትውፊትና ምሳሌ ዛሬ በሐዲስ ኪዳን ቀሳውስትና ዲያቆናት የሚለብሱት ልብሰ ተክህኖ አለ።

2. <u>የቄስ ልብስ</u>፡-

- <u>ቀሚስ</u>፡- ይህ በጥንት ዘመን አብደላከኒ የሚባል ቀሚስ ነበር፤ አሁን ግን ከማንኛውም ጌጥነት ካለው ጨርቅ የሚሠራ ነው። እርሱም በመጀመሪያ የሚለበስ ልብስ ነው። ቀሚስ በልክ እንዲሆንም ታዟል ፤ ከዚህ በተጨማሪ ረዥም እንደሆነ ማሳጠሪ ልክ እንደሆነ ሰውነትን ማጠንከሪያ የሚሆን መታጠቂያ / ዝናር/ አለው፤ የቅዳሴው መጽሐፍ ‹ ወእሥሮ በዝናር› ይላል።
- <u>ካባ ላንቃ</u>፡- መደረቢያው ልብስ ካባ ላንቃ ይባላል። ከካባው ጋር ለምድ አብሮ ተሰፍቶ ስለሚገኝ ነው ካባ ሳንቃ የተባለው። የለምዱ እግር / ዘርፍ/ በየቦታው እንደ ሳንቃ እየሆነ ስለሚወርድ ካባ ሳንቃ ተብሎአል።ይህም ልዩ ልዩ ቀለማት ካላቸው ጨርቆች የሚሠራ ነው። ግን በተቻለ መጠን በሙካሽ የተሠራ ሊሆን ይችላል። ወይም ወርቀ ዘቦ ይባላል። ወርቅና ሐሩ አብሮ ተፈትሎ ከተሠራ ጨርቅ ሊሰፋ ይችላል። ወይም ልሙጡ ማንኛውም ጨርቅ ሊሆን ይችላል።
- <u>ሞጣሕት</u>፡- በአንገት ተጠልቆ ፊት ለፊት የሚወርድ የደረት ልብስ ነው። ይህም በኦሪት ኤፋድ የሚባለው የአሮን ልብስ አምሳል ነው። የዚህም ጨርቅ ከላይ ከተጠቀሰው ዓይነት የሚሠራ ልብስ ነው።
- <u>ቆብ ወይም ቀጸላ ፥ ሕባኔ</u>፡- እስካሁን የቆየው ግን ቀጸላ ብቻ ተጎናጽፎ መቀደስ ነበር። በአሁኑ ዘመን ግን የተለየ ቆብ እየተሰፋ መነኩሴም ቢሆን ሕጋዊም ቢሆን ቆብ ደፍቶ መቀደስ ሥራዓት ሆኗል። ሆኖም የመነኩሴና የሕጋዊ ቄስ በቅዳሴ ጊዜ የሚደፉት ቆብ ቅርጹ ይለያያል ከቅዳሴ ውጪ ግን ቆብ ለመነኩሴ እንጂ ለቄስ አልታዘዘም።

3. <u>የዲያቆን ልብስ</u>

- <u>ቀሚስ</u>፡- እንደ ቄሱ ያለ ስለሆነ ሐተታው ያው ነው።
- <u>ለምድ ሳንቃ</u>፡- በቀድሞው ዘመን ቀሚሱ ለብቻ ለምዱ ለብቻ ይዘጋጅ ነበር ፤ አሁን ግን ለምዱ ከቀሚሱ ጋር አብሮ ይሰፋል ፤ ዲያቆኑ ያንን ይለብሳል።
- <u>ከፋይ ድግድጋት</u>፡- ከግብፅ ቤተክርስቲያን የተወሰደ ነው። ዲያቆናት አንዳንድ ጊዜ ለምድና ቀሚስ በመልበስ ፈንታ ቀሚስ ለብሰው በከፋይ መታጠቂያ በመስቀል ቅርፅ ስለሚታጠቁና ስለሚያደገድጉ ከፋይ ድግድጋት ይባላል። በአሁኑ ጊዜ ከቀኖና ውጪ የሰንበት ተማሪዎች ሲጠቀሙበት ዲያቆናቱ ግን እየተውት ነው።
- <u>አክሊል ወይም ቆብ</u>፡- በታላላቅ አድባራትና ገዳማት አልፎ አልፎ በገጠር አብያተ ክርስቲያናትም ዲያቆን አክሊል ወይም ቆብ ደፍቶ ይቀድሳል።

ለቅዳሴ አገልግሎት የሚለበሰው ልብስ ተክህኖ ነጭ እንዲሆን ሥርዓተ ቅዳሴ ያዝዛል። ሌሎች ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚለበሰው ልብስ ተክህኖ ግን የተለያየ ቀለም ቢኖረውም አይከለከልም።

4. <u>ማኅፈዳት</u>፡- አምስት የልብስ መጠቅሊያዎች / መሸፈኛዎች/ ናቸው። ብዙውን ጊዜ ከጥቁር ጨርቅ የሚሠሩ ናቸው። አንደኛው በጻሕሉ ሥር በታቦት ላይ ይነጠፋል ፤ ሁለተኛው በጻሕሉ ላይ ይነጠፋል፤ ጎብስቱ የሚጠቀለልበት ነው። ሦስተኛው የመሥዋዕቱ ልብስ ነው ፤ ቁመቱ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ሆኖ ይለብሳል ፤ አራተኛው ከሰሜን ወደ ደቡብ ሆኖ ይለብሳል ፤ አምስተኛው ከመስዕ / ሰሜናዊ ምሥራቅ/ ወደ ዐኤብ / ደቡባዊ ምዕራብ/ ሆኖ ይለብሳል።

ክርስቶስ በበረት ሲወለድ በጨርቅ መጠቅለሉንና በበለስ ቅጠል መሸፈኑን የሚያስታውስ ፥ በተለይም ዮሴፍና ኒቆዲሞስ በድርብ በፍታ የገነዙትን የሚያመለክት ምሳሌ ነው።

5. <u>መንጦላዕት</u>፡- በ 3 ቱም የመቅደስ በር የሚጋረዱ መጋረጃዎች ናቸው። እነርሱም ለመቅደስ ክብርን የሚሰጡ ናቸው። መጋረጃዎቹ የሚከፈቱበትና የሚዘጉበት ጊዜ አለ። በመጀመሪያ ቅዳሴ ማለትም ‹ ኦ እጉየ› ከሚለው ምዕዳን ጀምሮ እስከ ‹ ሚመጠን› ድረስ ይዘጋል ፤ ስገዱ ተብሎ ከታወጀና ፍትሐት ዘወልድና በእንተ ቅድሳት ሊጸለይ ከተከፈተ ጀምሮ እስከ ፍሬ ቅዳሴ ድረስ ይከፈታል። ከፍሬ ቅዳሴ እስከ ሦስተኛው ጸሎተ ፈትቶ ማለትም ‹ አርኅው ኖኃተ መኳንንት › ብሎ ንፍቁ ዲያቆን ማሳሰቢያ እስከሚሰጥ ድረስ ይዘጋል። ‹ አርኅው ኖኃተ› ሲል ይከፈታል ፤ በቁርባን ጊዜ ይዘጋል።

የመጀመሪያው ቅዳሴ የሚባለው ግባተ መንጦላዕት ወይም ሥርዓተ ግብፅ የሚባለው ነው ፤ ይኸውም ‹ ኦ እጉየ› ከሚለው ምዕዳን ጀምሮ እስከ ‹ ሚ መጠን › ያለው የንሰሐና የሥርየተ ኃጢአት ጸሎት የንዋያተ ቅድሳት መባረኪያ ጸሎት ነው። ሁለተኛ ቅዳሴ የሚባለውም የንባብ ወይም የትምህርት ቅዳሴ ወይም ሥርዓተ ቅዳሴ የሚባለው ነው። ይኸውም ‹ ሚ መጠን› ከሚለው ጀምሮ እስከ ጸሎተ ሃይማኖት ወይም እስከ ፍሬ ቅዳሴ ድረስ ያለው ቅዳሴ ነው።

ሦስተኛ ቅዳሴ የሚባለው ‹ ፍሬ ቅዳሴ› የሚባለው ዋናው የቁርባኑ ጸሎትና ቡራኬ ያለበት ቅዳሴ ነው።

6. <u>ልብሰ ታቦት / መጎናጸፊያ/</u>፡- ይህ ለአከብሮተ ሥጋውና ደሙ በቅዳሴ ጊዜ መንበሩ /መሠዊያው/ የሚለብሰው . ታቦት በወጣ ጊዜ የሚጎናጸፈው ነው፤ ስለዚህ ስሙ መጎናጸፊያ ተባለ።

3.7 ሌሎች ንዋያተ ቅድሳት

ሀ. <u>መንበረ ታቦት</u>፡- መንበር የታቦት ወይም የጽላት መቀመጫ ዙፋን ነው። ‹ ወይዑዱ ታቦተ› ሲል መንበሩን ይዙሩ ማለቱ ነው። መሥዋዕተ ኦሪት ይቃጠልበት፤ ይሠዋበት በነበረው ፈንታ መንበሩ የገባ ስለሆነ ከታቦቱ ጋር መሥዋዕት ይሰዋል። መሠዊያ ማለት ነው።

ለ.<u>ጻሕሉ</u>፡- የሥጋው ማስቀመጫና ማክበሪያ ነው ፤ ይኸውም ከወርቅና ከብር ፥ ከናስና ከብርት የሚሠራ ነው። የተለየ ቅርፅ የተለየም ምልክት ያለው ነው።

ምሳሌው ግን ክርስቶስ የተወለደበት ግርግም ወይም የበረት ምሳሌ ነው። እንዲሁም ጻሕሉ የመቃብሩ ምሳሌ ነው። < አንበረነ ዲበ ዝንቱ ጻሕል በአምሳለ መቃብር..... ይላል ሥርዓተ ቅዳሴው።

ሐ. ጽዋዕ፡- ይኸም የክርስቶስ ክቡር ደም የሚቀርብበት ንዋየ ቅዱስ ነው። ከወርቅ * ከብር ፣ ከመዳብ ከከነሃስ ፣ ከብረት የሚሠራ ነው። ይኸም በዕለተ ሐሙስ ክርስቶስ < ይህ ደሜ ነውና ሁላችሁ ጠጡት> ብሎ የሰጠን ጽዋ የሚያስታውስ ነው። / ማቴ 26*27/፤ እንዲሁም መለእክት ክርስቶስ በተሰቀለና ደሙ በፈሰሰ ጊዜ በብርሃን ጽዋ እንደ ተቀበሉት ጥንታዊ ትውፊት ያስረዳናል የዚህ ምሳሌ ነው።

መ. ዕርፊ መስቀል፡- ማንኪያ ዓይነት የሆነ የክርስቶስን ደም ለማቀበል የሚገለግል ንዋየ ቅዱስ ነው። ይኸውም ጽዋው ከተሠራበት ቁስ የሚሠራ ሲሆን በደሙ መያዣ በኩል በጣም ጎድጎድ ያለ ልዩ ቅርጽም ያለበት ሲሆን ወደ እጅ መያዣው መስቀል ያለበት ነው።ይህ የሱራፊ ጉጠት ምሳሌ ነው ፤ የሱራፊ ጉጠት ፍም ይዟል ፤ እርፈ መስቀልም የመለኮትን እሳታዊ ደም ይይዛል ፤ የሱራፊ ጉጠት የያዘው ፍም የኢሳያስን ከንፈር ከለምጽ አድኖአል ፤ ደሙም ምእመናንን ከኃጢአት አድኖአል።

ሠ.ዐውድ፡- በድርገት ጊዜ ጻሕል የሚቀመጥበት ፡- ሰፋ ያለ ጻሕል ነው። ሥጋው እንዳይነጥብ / እንዳይወድቅ/ መጠበቂያና ሰፋ ኅለም ከበርም ብሎ እንዲታይ በማለት የተደረገ ነው። እርሱም የሚሠራው ከብርት ' ከነሃስ ' ከእንጨትም ነው። ስሙ እንደሚያመለክተው አደባባይ ማለት ስለሆነ ጌታችን የተፈረደበት የጲላጦስ አደባባይ ምሳሌ ነው።

ረ. አኅበር፡- በዐውዱ ላይ የሚደፋ አራት ማዕዘን ሦስት እግር ያለው እንጨት ወይም ብር ሊሆን ይችላል። ይኸውም ሥጋውን ልብሱ እንዳይነካው ከፍ አድርጎ ልብሱን የሚዝ የሚከላከል ነው። እንዲሁም መጎናጸፊያውን ጎበብ አድርጎ ይዞ ከብር የሚሰጥ ነው።

ሰ. ጽንሐሕ፡- የዕጣን ማሳረጊያ ነው ፤ ይኸውም ከወርቅ ፣ ከብር፣ ከብረት ይሠራል። በኦሪት የወርቅ ማዕጠንት እንዲሠራ ለሙሴ እግዚአብሔር ያዘዘው ነው ፤ አሁንም በዚያ ምሣሌ የሚሠራ ነው።

ሸ. መሶበ ወርቅ፡- ኅብስት ቁርባኑ ከቤተልሔም ወደ መቅደስ የሚመጣበት ነው። መሶበ ወርቅ ከሰንደዶ ከአክርማና ከአለላ' ከወርቅ ' ከብር ከሌሎችም ማዕድናት የሚሠራ ነው። የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ነው።

ቀ.ቃጭል / ቃለ ዐዋዲ/ ወይም መረዋ፡- በቅዳሴ ጊዜ የሚቃጨልና ድምጽ የሚሰጥ ንዋይ ነው። ቃጭል ወደ ቅዳሴ ሲገባ ' ዓኡ ንዑስ ክርስቲያን ሲባል ' በእግዚኦታ ጊዜ ' ድርገት ሲወርድ ይቃጨላል። በዚህም ጊዜ ትልቁ የቤተክርስቲያን ደወል ይደወላል።ቃጭል በቅዳሴ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በሰሞነ ሕማማት ደወልን ተክቶ ይመታል። በጸሎትና በምህላ ላይ ይቃጨላል።

3.8 የማኅሌት መሣሪያዎች

የማኅሌት መሣሪያዎች ስምና ዓይነት

ሀ. ከበሮ፡- ከበሮ በቁሙ ንዋየ ማኅሌት ፣ አታሞ ፣ ነጋሪት ፣ ስለ ክብረ በዓል የሚመታ ፣ ክብራዊ ትእምርተ

ክብር ፣ ጫሂ ፣ ተሰሚ ማለት ነው። < ሰብሕዎ በከበሮ> < ንሥኢ ከበሮኪ> < መሰንቆ ወከበሮ> ይላል።

/ መዝ 150 ፤ ኤር 38.4 ፤ ዳን 3.10 ፤ ኢሳ 5.12/ ከበሮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትውፊትና ምሳሌነት አለው።

እስራኤል ባሕረ ኤርትራን ከተሻገሩ በኋላ የሙሴና የአሮን እኅት ማርያም ከበሮ እየመታች ዘምራለች / ዘጸ 15.20/።

ነቢዩ ዳዊትም ‹እግዚአብሔርን በከበሮ በማኅሌት አመስግኑት› ብሎአል/ መዝ 150 *4/

በሌላም ቦታ ‹ለያዕቆብ አምላክ እልል በሉ ፤ ዝማሬውን አንሱ ፥ ከበሮውም ስጡ› ይላል /መዝ 80.2/።

ዳዊትና ሠራዊቱም ታቦተ ጽዮንን ከአሚናዳብ ቤት በአመጡ ጊዜ ዳዊትና የእሥራኤል ቤት ሁሉ በቅኔና በበገና በመሰንቆና በከበሮ በነጋሪትን በጽናጽል በእግዚአብሔር ፊት ሙሉ በሙሉ ኃይላቸው ይዘምሩ ነበር/ 2 ኛ ሳሙ 6.5/።

‹ ዮዲትም ፈጣሪያችንን እግዚአብሔርን ከበሮ እየመታችሁ አመስግኑት ብላለች /ዮዲት 16.2/።

ከበሮ በክብት ቆዳ ተጠፍሮ ከእንጨት ወይም ከብር የሚሠራ የዜማ መሣሪ ነው ' ከበሮ ለደስታም ሆነ ለኃዘን ' በድል ቀን መታሰቢም ሆነ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት ሲከብር የሚመታ መሣሪያ ነው። ከበሮ በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን ዘመን ተፈላጊነቱ እጅግ የላቀና የተወደደ ነው ፤ ከበሮ ከነ ጥቅሙና ከነአገልግሎቱ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በምዕራፍና በአንቀጽ ተጠቅሶ ይገኛል። / ዘጸ 15.20 ፤ መዝ 150 .4 ፤ 80.2 1 ኛ ሳሙ 18 .6-8 ፤ መዝ 149*3 ፤ 2 ኛ ሳሙ 6*5/።

ለ. <u>ጸናጽል</u>፡- ጸንጸለ መታ ከሚለው ግስ የተገኘ ነው፤ ጸናጽላት በሚልበት ጊዜ ብዛትን ' ጸናጽል ሲል ደግሞ ነጠላን የሚያመለክት ሲሆን ትርጉሙም ሻኩራ ' ቃጭል እንደ ማለት ነው። ጸናጽል ከናስ ወይም ከብርና ከሌላም ማዕድን ሊሠራ የሚችል የዜማ መሣሪያ ነው። ጸናጽል ያማረ ድምጽ ያለው ሆኖ መልክና ልዩ ጌጥ አለው /መዝ 150.5/።

በጥንት ዘመን ግብፃውያን እግዚአብሔርን ያመሰግኑበት እንደነበር ይናገራል ፤ አሠራሩ ወይም መልኩ እንዲህ ነበር ' ላዩ ቀስተደመና ይመስላል ፤ ከታች መጨበጫው አንድ ሆኖ የላም ምስል ነበረበት ፤ የዚህ ምስል በአሁኑ ጊዜ በፈረንሳይ አገር ሳሩስ በሚባል መጽሐፍ ላይ ተስሎ እንደሚገኝ ይነገራል። በተጨማሪም በዚህ መሣሪያ ዕብርውያንም ይገለገሉበት ነበር። በእኛ ቤተክርስቲያን የምንገለገልበት ጸናጽል ላዩ ቀስተደመና መምሰሉ ‹ እሠይም ቀስትየ በውስተ ደመና› /ዘፍ 9*12/ ብሎ እግዚአብሔር ለኖኅ ያሳየው የምህረት ቃል ኪዳንመታሰቢያ መሆኑን አራቱ ዘንጎች የአራቱ ባሕርያተ ሥጋ ‹ የመሬት ፥ የእሳት ፥ የነፋስና የውኃ ፥ ቅጠሎች የፍጥረታት ምሳሌዎች መሆናቸውን ፥ ይኸውም ከአራቱ ባሕርያት የተፈጠሩትን ፍጥረታት ሁሉና ‹ ሰውንም አላጠፋም› ብለህ ቃል ኪዳን ሰጥተሃልና ኪዳነ ኖኅ አስብልን ፤ በኃጢአታችን አታጥፋን ብለው ማመስገናቸውን የሚያመለክት ሲሆን መሰላሉ ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ ያየው መሰላል ምሳሌ ነው። /ዘፍ 28-11-13/ በግራና በቀኝ ባሉት አምዶች መካከል ያሉት ሁለት ቀጫጭን ዘንጎች ወይም ጋድሞች የመወጣጫው አምሳል ወይም ምሳሌ ' በእዚህ ላይ የተንጠለጠሉት ቅጠሎች በመሰላሉ ላይ ይወጡ ይወርዱ የነበሩ የመላእክት ምሳሌ ' በግራና በቀኝ የቆሙት ዓምዶች የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ምሳሌ ' ሁለቱ ጋድሞች የፍቅረ እግዚአብሔርና የፍቅረ ቢጽ ምሳሌ ናቸው።

ጸናጽል በማኅሌት አገልግሎት በኩል በሥራ ላይ ሊውል የሚችለው ከከበሮ ጋር ነው እንጂ ብቻውን ሊሆን ወይም ሊያገለግል አይችልም።

የጸናጽል ጥቅምና ሙያ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ ይዞ ይገኛል፤ ይኸውም ‹ ወንበሩ ጸናጽል ዘወርቅ አርባዕተ ምዕት * አራት መቶ የወርቅ ጸናጽል ሠሩ ፤ የብር ጸናጽል ፤ በጸናጽል የሚዘምሩ በከበሮም የሚያሸበሽቡ ነበሩ ፤ ድምፁ ባማረ ጸናጽል ማለት ነው። ‹

ጸናጽል ብሩር ' እለኒ በጽናጽልእለኒ በከበሮ ' ጸናጽል ዘሠናይ ቃሉ› የሚሉ ጥቅሶች በየአንቀጹ ተጠቅሰው ይገኛሉ። / 2ኛ ዜና መዋ. 29.25 ፤ 1ኛ ዜና መዋ 15.16-19 ፤ 2ኛሳሙ 6.5 ፤ 1ኛዜና. መዋ. 15.8 ፤ 2ኛዜና መዋ. 5.13 ፤ 1ኛ ቆሮ 15.1-3/።

ሐ. <u>መቋሚያ፡-</u> መቋሚያ ማለት መደገፊያ መመርኮዣ ማለት ነው። ይኸውም በምርኩዝነቱና በመደገፊያነቱ ሊያገለግል የሚችለው ለካህናት ብቻ ሳይሆን በቤተክርስቲያን ቆመው ለሚያስቀድሱና ለሚጸልዩ ወንዶችና ሴቶች ምእመናን ጭምር ነው። እግዚአብሔር ለአዳም ተስፋ አድርጎ የሰጠው የመስቀል ምሳሌ በመሆኑ ቅዱስ ያሬድና አባ እንጦስን በማኅሌትና በጸሎት ወይም በሰዓታት ጊዜ መቋሚያ እንዲያዝ ወይም በመቋሚያ አገልግሎት እንዲፈጸም አድርገዋል። በመሆኑም ቅዱስ እንጦስ በጸሎት ጊዜ ቅዱስ ያሬድ በማኅሌት ጊዜ መቋሚያ ተጠቅመዋል። ሙሴ ባሕረ ኤርትራን የከፈለበት በተሻገረም ጊዜም ተአምራት ያደረገበትን ትእምርተ መስቀል ያለበት መቋሚያውን በትከሻው ይዞ በእስራኤል መካከል ወዲያና ወዲህ በማለት ‹ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ› እያለ ያመሰገነውን ምሥጋና የሚያሳስብ እንደሆነም ሊቃውንቱ ይናገራሉ። መቋሚያ በሴቶችና በወንዶች ምእመናን እጅ በሚውልበት ጊዜ አገልግሎቱ ያለው ከላይ እንደተገለጸው ለመደገፊያ ብቻ ነው። መቋሚ በማኅሌት ላይ ገብቶ መዘምራን እጅ በሚውልበት ጊዜ ግን የተለያዩ አገልግሎቶችን ይሰጣል። ይኸውም መደገፊያ ከመሆኑም ጋር ለማኅሌቱ ሥራ መሪ ቀኝ ሆኖ ያለ ከበሮና ያለ ጸናጽል በዝማሜ ብቻ ያገለግላል። መዘምራን በአጽሕሶ / በማስረገጥ/ ጊዜ መቋሚያውን በትከሻቸው ላይ ተሸክመው ነው ከወዲያና ወዲህ የሚያሸበሽቡት። ይኸው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ‹ ዘኢያረ መስቀል ሞትየ ኢይክል ይፀመደኒ › ያለው ያመለክታል።ከዚህም በስተቀር ቀደም ሲል እንደገለጽነው ሙሴ ከኤርትራ በሕር እስራኤልን በሰላም ይዞ ከተሻገረ በኋላ እኅቱ ማርያም ከበሮ በአንገቷ ይዛ * በአዋጅ ስትመታ እሱ መቋሚያ በትከሻው ተሸክሞ በእስራኤል መካከል እያሸበሸበ ይዘምረው የነበረውን መዝሙር ያስታውሳል። /ዘጸ 15*20/። የመቋሚያ ርዝመቱ አንድ ሜትር ተኩል ወይም ከዚያ በላይ ወይም ከዚያ በታች እንደሰውየው ቁመት ሊሆን የሚችል ሲሆን መጨበጫው እንጨት ሆኖ መደገፊያው ከብረት ወይም ከነሐስ ወይም ከብር ወይም ከወርቅ ወይም ከቀንድ የተሠራ የሚያምር ቅርጽ ያለው ነው። ቅርጹም የተለያየ መልክ ያለው ስለሆነ በሥዕሉ ላይ መመልከት ይቻላል።

3.9 <u>ለቤተክርስቲያን የሚደረግ ክብርና ጥንቃቄ</u>

ለጸሎትና ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል ወደ ቤተክርስቲያን በሚኬድባቸው ዕለታት እንዲሁም በጾምና በሰንበት በበዓላት ቀኖችም ባልና ሚስት በተራክቦ መገናኘት ክልክል ነው። በመኝታ የተገናኙ ወደ ቤተክርስቲያን በዕለቱ አይገቡም ፥ ወደቤተክርስቲያን ባይሄዱም በዓላትንና አዕጽዋማትን ሊጠብቁ ይገባል።/ ዘጸ 19.15 ፤ 1ኛ ቆሮ 7.5-7 ፤ ኩፋ 30.12/ ሴት የወር አበባዋ ሲመጣ እስከ ሰባት ቀን ድረስ ስትወልድ ወንድ ከወለደች እስከ 40 ቀን ሴት ከወለደች እስከ 80 ቀን ድረስ ወደ ቤተክርስቲን እንዳትገባ ክልክል ነው። ከዚህ በኋላ ግን ገላዋን ታጥባ ትገባለች /ዘሌ 12.1- ፥ 15.19-28 ፤ ፍት .መን 6' ዘኂቅያ 29/።

ወንወድ ሕልመ ሌሊት /ዝንየት/ ከመታው በዕለቱ ወደ ቤተክርስቲያን አይገባም። በማግስቱ ገላውን ታጥቦ ይገባል። / ዘሌ 15.2-18/ ወደ ቤተክርስቲያንም ከገቡ በኋላ በጸጥታ የሚነበበውን የሚተረጎመውን መስማት ተሰጥኦ መቀበል ይገባል ፤ ወሬ ማውራት ማውካካት መንጫጫት ነውር ነው ክልክል ነው።

ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል ሦስት ትርጉም አለው፡-

ሀ. <u>ለአምልኮተ እግዚአብሔር የተሰበሰቡ ምእመናንን የሚያመለክት ነው</u>። ‹ በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ትጠብቁ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ› ይላል። / የሐ .ሥ. 20.28 ፤ 14.3 ፤ 1 ኛ ቆሮ 16.19/።

ለ. <u>ጉባኤ ቤተክርስቲያን /ሲኖዶስ /ነው፡-</u> ‹ እነሱን ባይሰማ ለቤተክርስቲያን ንገር › ይላል / ማቴ 18.17/ ለሲኖዶስ ንገር ማለት ነው።

ሐ.<u>ሕንፃ ቤተክርስቲያን ነው</u> ፡- ‹ ለዘለዓለም ስሜ በዚያ ያድር ዘንድ ይህን የሠራኸውን ቤት ቀድሻለሁ ፤ ዓይኖቼና ልቤም በዘመኑ ሁሉ በዚያ ይሆናሉ › ብሎ እግዚአብሔር ለሰሎሞን ነግሮታል። / 1 ኛ ነገ 9.3/።

ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ደም ስለተዋጀች ክብር አላት ፤ ጥንቃቄም ይደረግላታል ፤ የቤተክርስቲያን ባለ ቤት እግዚአብሔር ስለሆነ በጥንቃቄ ትጥበቃለች ፡ እግዚአብሔር ለካህናት የጥበቃውን አደራ ሰጥቷልና። ካህናት የተሸሙት ቤተክርስቲያን ለመጠበቅ ፤ ለቤተክርስቲያን ጥንቃቄ ለማድረግ ነው። /የሐ. ሥ. 20.20/። ቤተክርስቲያን የካህናትና የምእመናን የጋራ ቤት ናት ፤ ስለሆነም ሁሉም በቤተክርስቲያን አገልግሎት የየራሳቸውና የማይተካ ድርሻ አላቸው። ቤተክርስቲያን የካህናትና የምእመናን ጉባኤ ስለሆነች ክብር አላት። በሃይማኖትና በቀኖና ጉዳይ ስልጣን አላት። ምእመናንና ካህናትን ትዳኛለች። በቀኖና ትቀጣለች ' በውግዘት ታሥራለች ' በጸሎት ፍትሐት ትፈታለች › ይህም ማለት ጎጥቡን ' መናፍቁን ከሐዲውን ታወግዛለች ተነሣሒውን ትፈታለች ማለት ነው።

ቤተክርስቲያን በቅዱስ አምላክ ቅድስና የተቀደሰች፡ ቅድስናውን የተቀበለች ፡ ቅድስናውንም ለማስተላለፍ የተመረጠች ቅድስት ስለሆነች ከርኩሰት ፤ ከርስሐት ትጠበቃለች ፡ ጥንቃቄም ይደረግላታል።

ቤተክርስቲያን በነቢያት በሐዋርያት መሠረት ላይ የታነፀች የክርስትና እምነት ተቋም ስለሆነች መሠረቷ በሲዖል ሠራዊት / አጋንንትና መናፍቃን / እንዳይናወጥ በካህናትና በምእመናን ጥበቃ እንክብካቤ ይደረግላታል።

ቤተክርስቲያን ለአምልኮተ እግዚአብሔር ተሰብስበን ጸሎታችንንና ምሥጋናችንን ለእግዚአብሔር የምናቀርብበት በጥምቀተ ክርስትና ከእግዚአብሔር በጸጋ የተወለድንበት ' ሥርየት ኃጢአትን የምናገኝበት ' ጸጋ መንፈስ ቅዱስ የተቀበልንባት ' በሥጋ ወደሙ የዘለዓለም ሕይወት የምናገኝባት' በንሰሐ በደላችንን አስወግደን ከእግዚአብሔር የምንታረቅባት የምሕረትና የድኅነት አደባባይ ስለሆነች እጅግ የከበረች የእግዚአብሔር ቤተመንግሥትና ቤተክህነት ናት።

እግዚአብሔር ልዩ ልዩ ጸጋውን ለማደል በቤተክርስቲያን በረድኤት ስለሚገኝ ቤተ እግዚአብሔር ትባላለች። ቤተ እግዚአብሔርም በመሆኗ ከነገሥታት አብያተ መንግሥታት የበለጠ ክብር አላት። ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ደም ስለ ተቀደሰች ከማንኛውም ርኩሰት እንድትጠበቅ ካህናት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ያደርጉላታል ማድረግም አለባቸው።

አብዛኛውን ጊዜ ቤተክርስቲያን ስንል በክርስቶስ የሚያምኑ ወገኖች ለጸሎት የሚሰበሰቡበት የተቀደሰው ቤት ማለታእንደመሆኑ እግዚአብሔር በጸሎተኞቹ መካከል ያለ መሆኑን ማወቅ አለብን ፤ ጌታም በቃሉ ታማኝ ሥለሆነ በመካከላችን እንደሚገኝ እርግጠኛ እንሁን። / ማቴ 18.20/

ሁኔቴው እንደዚህ ከሆነ እግዚአብሔር ወደ ቀደሰውና በጸሎተኞችም ወደ ሚገኝበት ወደ ቤተክርስቲያን የምንገባው እንዴት ነው ? ገብተንስ ምን ማድረግ አለብን ?

አንድ ሰው አንድን ትልቅ ባለሥልጣን ለመገናኘት ምክንያት ያገጠመው እንደሆነ ይሸቀጠቀጣል። ባለሥልጣኑ የሚገኝበትን ቤት ወይም ቢሮ በጣም ከማክበሩና ከመፍራቱ የተነሳ አካሄዱና አረማመዱ ይለወጣል ' ሰውነቱ ይሸማቀቃል፤

በመጽሐፈ ሲራክ 10.12 ላይ ‹ ዛሬ ንጉሥ ነገ ሬሣ› ተብሎ በተነገረው መሠረት ዛሬ በሕይወቱ በክብርና በመባዓረጉ ላይ ቢሆንም ነገ በሞት ወይም በሽረት ክብር የሚያጣውን ምድራዊ ገዥና እርሱ የሚገኝበትንም ቤትና ቢሮ እንደዚያ የምናከብር ከሆነ ዘለዓለማዊው ፈጣሪ የሚገኝበትንና አምልኮ እንዲቀርብበት የቀደሰውን ቤተክርስቲያን እንዴት ባለ ሁኔታ ማክበር እንደሚገባን እናስብ።

ወደ ቤተክርስቲያን ደርሰን ስግደት ካደረግን በኋላ በቤተክርስቲያን ቀስ ብለን ቦታችንን እንይዛለን። በዚህ ጊዜ ህዝብ ሊሳተፍበት የሚገባ የኅብረት ጸሎት ከሌለ የግል ጸሎታችንን ልንጸልይ እንችላለን። የኅብረት ጸሎት በሚካሄድበት ጊዜ ግን የግል ጸሎት መያዝ አግባብ አይደለም። ወደ ቤተክርስቲያን ከምንሄድባቸው ምክንቶች አንዱ በኅብረት ጸሎት ለመሣተፍ እንደመሆኑ በኅብረት ጸሎት ጊዜ የግል ጸሎት ማካሄድ የለብንም።

በቤተክርስቲያን ውስጥ ለጸሎት ተሰብስበን በምንገኝበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ስለአለን ኅብረት እንጂ አስተሳሰባችን ወደ ዓለማዊ ጉዳይ ማባከን ተገቢ አይደለም።ስለ ዓለማዊ ጉዳይ ለማሰብ ከቤተክርስቲያን ከወጣን በኋላ በቂ ጊዜ ይኖረናል። በቤተክርስቲያን የሚገኘው አብዛኛው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ኅብረት ጠብቆ በተመስጦ ሆኖ የሚጸልይበትና ምሥጋናውን ለእግዚአብሔር በሚያቀርብበት ጊዜ አንዳንድ ሰዎች በቤተክርስቲያን ውስጥ መሆናቸውን በአለማጤን የግል ጉዳያቸውን ሲወያዩ ይሰማሉ። ይህ በሚደረግበት ጊዜ በአንድ በኩል አጠገባቸው ሆኖ በተመሥጦ የሚጸልየውን ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ኅብረት ይበትኑበታል ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለግል ጉዳያቸው ሌላ በቂ ጊዜ ያላቸው ሆኖ ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረጊያ የሆነችውን ያቺን ጥቂት ጊዜ በማባከን አግባብ ባልሆነ መንገድ ለልዑል እግዚአብሔር መስጠት ከሚገባቸው ክብር ላይ ይቀንሳሉ። በዚህም የሚገኙትን ጸጋና በረከት ይቀርባቸዋል ወይም ይቀንስባቸዋል።

ቤተክርስቲያን የመሠለ እግዚአብሔር የቀደሰውና ክብሩን የሚገልጽበት ቦታ ብቻ ሳይሆን በጊዜያዊነት እንኳ ለአንዳንድ ቅን ታዛዦች የሚገልጽባቸው ቦታዎች ክብር የሚገባቸው መሆናቸውን ሲያመለክተን በኦሪት ዘጸአት 3*5 ላይ ለሙሴ ፥ በመጽሐፈ ኢያሱ 5*15 ደግሞ ለኢያሱ እነዚያ እነርሱ የቆሙባቸው ቦታዎች የተቀደሱ ስለሆኑ ጫማቸውን እንዲያወልቁ ተነገሮዋቸዋል። ዛሬም ወደ ቤተክርስቲን ስንገባ ጫማ የምነወልቀው በዚህ የቅድሳት መጽሐፍት ቀኖና መሠረት ነው።

ስለዚህ ፈጣሪ አምላክ የቀደሰውን * አምልኮተ እግዚአብሔር የምናከናውንበትና ምሥጢረ ሥጋዌው የሚነገረበትን ቤተክርስቲያን ማክበር ያለብን መሆኑን እናስተውል።

ቤተክርስቲያን የምትባረከውና ሜሮን የምትቀባው በኤጲስ ቆጶስ ነው። በዚህም ጸሎትና ቡራኬ እግዚአብሔር ይቀድሳታል። ከሌላም ቤት እንድትለይ ያደርጋታል። ነብዩ ዳዊት ‹ ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ ' እንዳትናወጥም እግዚአብሔር በመካከልዋ ነው ' እግዚአብሔር ፊት ለፊት ይረዳታል ይላልና ።/ መዝ 45*4-5/።

የቤተክርስቲያን ምሳሌዎቹዋ የሆኑት የኖኅ መርከብ ፥ ደብተራ ኦሪት ' የሰሎሞን ቤተ መቅደስ በተሰፋ ከብረው ነበር ፤ አማናዊት ቤተክርስቲያን ግን የከበረችው ' የተቀደሰችው ፍፁሜ ተስፋ በሆነው በአማናዊ አምላክ ደምና ስም ነው።